# ኢትዮጵያን ከዉጭ የሚከሱት

# እነማን ናቸዉ?

# ለምን ይሆን?

# በምን ጉዳዮች?

አገራችን ኢትዮጵያ ለአያሌ ዓመታት ከተለያዩ ዉጭ ሃይሎች በሚሰነዘሩባት መሰረተቢስ በሆኑ አሉባልታ ክሶች ስትወቀስ ኖራለች። ኢትዮጵያን የሚከሷት እነማን ናቸዉ? ለምንድነዉ? እና በምን ጉዳዮች? የሚሉትን ጥያቄዎች በጥሞና ማጤንና መሰረታቸዉን ማወቅ፣ ክሶችን ለመመከትና ለማክሸፍ እንድሁም በአገር ዉስጥ ያለዉና ዓለም ዓቀፍ ማህበረሰብም የአገራችንን ትክክለኛና እዉነተኛ ገፅታ አዉቆ ከአገራችን ጎን እንድሰለፍ ለማድረግም ወሳኝ ሚና ይኖረዋል።

ኢትዮጵያን ከወሰነ ድንበሯ ዉጭ ሆነዉ ከሚከሱት ሃይሎች ዋነኛዎቹ የኒዮ-ልበራል ፖለትካ ኢኮኖሚ ወይም ገበያ አክራርነት ሪዮተ-ዓለም ፅንሰ ሃሳብ አቀንቃኞች (neo-liberal political economy ideology fundamentalists and their institutions) በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። ከእነዚህ ተቋማት ዉስጥ ዋነኛዎቹ የሰብዓዊ መብት ተሚጋች ባይ አስመሳይ የደሃ አገር መንግስታት ብቻ ከሳሾች(INTERNATIONAL CRIMINAL COURT , HUMAN RIGHTS WATCH, AMENSTY INTERNATIONAL)፣የተወሳሰበ የሪዮተ ዓለም ሃሳቦችን አንግቦ ምርምሮችንና ጥናቶችን የሚያካህዱ የምርምር ተቋማት፣ዩኒቨርሲቲዎች እና ምሁራን ፣ አንዳንድ ብዙሃን መገነኛዎች እና የመሳሰሉት ናቸዉ።

## *ኢትዮጵያን የሚከሱት ለምን ይሆን?*

አንደኛ በግንባር ቀደምትነት የሚነሳዉ ጉዳይ ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ የምትከተለዉ ልማታዊ፣ ዴሞክራሲያዊና አብዮታዊ ፖለትካ ኢኮኖሚ ርዮተ ዓለም እያደገና በዓለም

ዓቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ በሄደ ቁጥር ለኒዮ-ልበራል ፖለትካ ኢኮኖሚ ወይም ለገበያ አክራርነት ሪዮተ-ዓለም ፅንሰ ሃሳብ ፀር ይሆናል የሚል መላምትና የተሳሳተ አመለካከት ስላደረባቸዉ ነዉ፡፡

ሁለተኛ የኢትየጦጵያ መንግስት የሚከተላቸዉ የምልዓተ-ህዝቡን ተጠቃምነት የሚያረጋግጡና ስር ነቀል ለዉጥ ሊያመጡ የሚችሉ ፖሊሲዎች፣ እንደ ሌሎች ኒዮ-ሊበራል አገራት ፖልሲዎች ግለሰቦችንና ጥቂት ተቋማትን ብቻ የነጠጡ ሀብታሞች አድርገዉ ሰፊዉን ህዝብ የሚደፈጥጡ ባለመሆናቸዉና የኢትዮጵያን አንጡራ ሀብት በዓለም ዓቀፍ ድንበር ዘለል ድርጅቶቻቸዉ(Multi- national corporations) አማካኝነት ገብቶ ለመዝረፍ፣ ለማስዘረፍና ለመዝበር እንድሁም የኢትዮጵያን አገር በቀል ተቋማትን ለማቅጨጭ የኢትዮጵያ መንግስት በር ከፍቶ ስላልሰጣቸዉ ይከስሳሉ፡፡ በአንድ ኒዮ-ልበራል ፖለትካ ኢኮኖሚ ወይም በገበያ አክራርነት ሪዮተ-ዓለም ፅንሰ ሃሳብ አቀንቃኝ ኢኮኖሚስት ጆሆን ዊልያምሰን ተፈበርኮ የታዳጊ አገራት ተጨባጭ ሁኔታ ሳያገናዝብ መላዉ ታዳጊ አገራት እንደወረደ እንድጠቀሙ ተብሎ የተቀመጠዉን የዋሽንግተን ስምምነት (Washington consensus) በመባል የሚታወቀዉን አስርቱ የፖሊሲ ትዕዛዛት ኢትዮጵያ ከተጨባጭ ሁኔታዋ ጋር ስለማይጣጣም ሙሉ በሙሉ ስለማትተገብር የምዕራባዊያን ምሁራን ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ይከስሷታል፤

ሶስተኛ እነዚህ ኢትዮጵያን ከዉጭ  የሚከሱት ምዕራባዊያንና ተቋማቶቻቸዉ በኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉ ፖለትካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጨባጭ ሀቆችን(Realities on the ground) ስላልተገነዘቡ ነዉ፡፡ ያለምንም ተጨባጭ ሁኔታዎች ግንዛቤ፣በምርምርና ትንተና ላይ ብቻ ተመርኩዞ  በሚመስላቸዉ መላምት በአገራቸዉ ቢሮ ዉስጥ ቁጭ ብሎ ለኢትዮጵያ የሚበጀዉን ፖሊሲ አቅጣጫ አዉቃለሁና እኔ የሚላችሁን ተግብሩ  ማለት እብደት ነዉ፤

አራተኛ ኢትዮጵያን የሚተቹበት ጉዳይ  ቻይና እና ህንድ በአፍሪካ የሚያደርጉትን ጂኦፓለቲካዊ መስፋፋት የሚቃወሙ ሀገራት ጉዳዩን የተለየ ስዕል በመስጠትና ከመሠረታዊ ጥቅማቸው በመነሳት የተለያዩ ቲንክ ታንክ ቡድኖችን አቋቁሞ በህንድ እና ቻይና አሉታዊና አፍራሽ ቅስቀሳዎችን በማድረግ ኢንቨስተሮች ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመጡ ለማድረግ እየሰሩ እንደሆነ እንዲሁም በቅርብ በፀደቀው የUS

consolidation or appropriation Bill ላይ ሀገራችንን ይጎዳሉ ያሏቸዉን አንቀፆች ለማካተት ላይ ታች ስሉ መከረማቸዉ አስገራሚ ነዉ። ቻይናና ህንድ በኢትዮጵያና አፍሪካ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ መጠነ ሰፊ የሆነ የመሰረተ ልማት፣ኢንቨስትሜንትና ንግድ መስፋፋትን ከማምጣትና እርስ በርስ በመደጋገፍ ቢዝነስ ከመስራት የዘለለ አይሆንም፤ መሆንም የለበትም። ይህ የቻይናና ህንድ ተሳትፎ ኢትዮጵያ የሚልኒየም ልማት ግብና የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካት ወሳኝ ሚና ይጫወታል፤ ስለዚህ ከቻይናና ህንድ ጋር የሚደረግ ግንኙነት ከርዮተ ዓለም ቁርኝነት የፀዳ ነዉ ማለት ይቻላል።

*__ኢትዮጵያን ከዉጭ የሚከሱት በምን ጉዳዮች ይሆን?__*

1/ በሰብዓዊ መብት አያያዝ ፡- በኢትዮጵያ ታሪክ ከመቼዉም ጊዜ በላይ የሰብዓዊ መብት አያያዝ ተሻሉና ተስተካክሎ የሚታይበት ጊዜ አሁን ቢሆንም የዜጎቻቸዉን እያንዳንዱን እንቅስቃሴ በስለላ መረብ ዉስጥ አስገብተዉ የግለሰቦችን መብት በአደባባይ የሚጥሱ አገራትና ተቋማት፣ድንበር አልፈዉ በአንድ ሉዓላዊ አገር ግዛት ዉስጥ የሰብዓዊ መብት መጣሻ ማዕከል ገንብተዉ ሰብዓዊ መብትን የሚጥሱ እና ከምድረ-ገጽ የሚሰርዙ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ፈጻሚዎችም ይከሱናል፡፡ የከሰሰ ለመከሰስ፣ የተከሰሰ ለመክሰስ፣ ለሁሉም ጊዜ አለዉ፡፡ ከእኛ የሚጠበቀዉ ዋናዉ ቁም ነገር ብሄራዊ መግባባትና አንድነት በመፍጠር የአገራችንን ጥቅም ለማስጠበቅ በአገኘነዉ አጋጣሚ ሁሉ ዘብ መቆም ነዉ።

2/ የመሬት ንጥቂያ (land grab or land for sale) በኢትዮጵያ ህገ-መንግስት አንቀጽ 40/3 ላይ በግልጽ የተቀመጠዉን “የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ ነዉ፤ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ንብረት ነዉ።” የሚለዉን ሀሳብ ራሳቸዉ የሻሩ እስኪመስል በኢትዮጵያ መሬት ከገበሬዎች እየተነጠቀ ለባለሃብቶችና ለዉጭ እንቨስተሮች እየተቸበቸበ ነዉ የሚሉ ወገኖች ተበራክቷል። ይህ ወሬ ከእዉነት የራቀና መሰረተ-ቢስ ፕሮፓጋንዳ ነዉ። ለምሳሌ የOakland institute እና መሰል የመብት ተሟጋች ድርጅቶች የሚያነሱት የጋምበላ እና ደቡብ ኦሞ መሬት ጉዳይ ክስ በጉያዉ የርዕዮተ ዓላማዊ ፅንሰ-ሃሳብ ያነገበ የዉሸት ክስ መሆኑ ግልጽ ነዉ። የልማት ፕሮጀክቶች በህዝብና ህዝብ በጎ ፈቃደኝነት ላይ ብቻ ተመስርተዉ

የሚካሄዱ እንጂ በፍፁም ህዝብን በማፈናቀል የሚፈፀሙ አይደሉም። በደቡብ ኦሞና ጋምበላ የሚገኙ ነዋሪዎች እየተካሄደ ካለዉ ዘርፈ ብዙ ልማት እንቅስቃሴ በተጨባጭ መንገድ፣መብራት፣ ዉሃ፣ ት/ቤት፣ የጤና አገልግሎት ወዘተ እየተጠቀሙ ይገኛሉ።

3/ ሌላዉ ኢትዮጵያን የሚከሱበት ጉዳይ የሚድያ (ፕሬስ) ነፃነት በተመለከተ ነዉ። የኢትዮጵያ መንግስት በሚድያ ሙሉ ነፃነት የሚያምንና ፕሬስ ነፃነትን ህገመንግስታዊ መሰረት ሰጥቶ የሚያስከብርና የሚያከብር ሆኖ ሳለ የሚድያ ነፃነት በኢትዮጵያ ተመናምኗል የሚሉ ወገኖቻችን የኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀፅ 29/3 “የፕሬስና የሌሎች መገነኛ ብዙሃን እንድሁም የስነጥበብ ፈጠራ ***ነፃነት ተረጋግጧል***።” የሚለዉን አንኳር ሀሳብ ያልተገነዘቡና አቅጣጫን የሳቱ ናቸዉ። እንድያዉም አንዳንዶቹ ህጎች በዲሞክራሲ ካደጉት አገራት ተሞክሮ የተቀመሩና ቃል በቃል የተቀዱ ናቸዉ፤ ነገር ግን በኢትዮጵያ አንጻር ሲተነተኑና ሲናገሩ ያጣምማሉ፤ ያብጠለጥላሉም። ችግሩ ከህጎች ትክክል ካለመሆን የመነጨ ሳይሆን ከርዮተ ዓለም ፖለትካ ንግድ ከማትረፍና መክሰር ትንታኔ የመነጨ ነዉ።

4/ በፀረ-ሽብር አዋጅ፡- ስለሰዉ ልጅ እኩልነት ታግሎ አፓርተይድ ስርዓትን ከደቡብ አፍርካ ጫንቃ ላይ ያወረደዉን ኔልሰን ማንደላን ጭምር በሽብርተኝነት ፈርጆ የነበሩ አገራትም ኢትዮጵያ ዜጎችን በፀረ-ሽብር ህጓ አማካኝነት እያሰረች ነዉ ብለዉ ይከስሳሉ። በሽብር ጉዳይ ተከስሶ የታሰሩ ግለሰቦች በአደረጉትና በፈፀሙት ሽብር ተግባር በፍርድ ቤት ዉሳኔ ብቻና ብቻ የታሰሩ እንጂ ለፖለትካ ትርፍ ተብሎ የታሰሩ አይደሉም።

5/ በፕራይቨታይዜሽን ጉዳይ የሚከሱት ክስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና መልኩን እየቀያየረ እንደ አዲስ የሚታይ መሆኑ በጣም የሚገርም ነዉ። ያደጉት አገራት በመንግስት ባለቤትነት ስር የነበሩ ድርጅቶችንና ተቋማትን ወደ ግሉ ዘርፍ ለማዘዋወር ከሁለት መቶ ዓመት በላይ እንደፈጀባቸዉ ከታርክ ማህደር መረዳት ይቻላል። እስካሁንም ከመንግስት እጅ ያልወጡ ድርጅቶች አሏቸዉ። ወደ

ኢትዮጵያ ሲመጣ በአንድ ጀምበር ሁሉንም ነገር ወደ ግሉ ዘርፍ አዘዋዉሩ ብለዉ የሚከሱት ያለዉን ተጨባጭ ሁኔታ ስላልተገነዘቡ ነዉ። ኢትዮጵያም ቴሌኮሚዩኒኬሽን፣መብራት፣ዉሃ፣ መንገድ የመሳሰሉትን ወደ ግሉ ዘርፍ ለማሸጋገር ተገቢዉን ዝግጅት ታደርጋለች ፤ በተገቢዉ ግዜ ሁኔታዎች ስፈቅዱና የምልዓተ ህዝቡን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አካሄድ ወደ ግሉ ዘርፍ ታስተላልፋለች።

ከላይ በጥቂቱ የተጠቀሱትን  መሰረተ-ቢስና ከእዉነት የራቁ ተቀባይነት የለላቸዉን ክሶች በዓላም ዓቀፍ ደረጃ በማራገብ የኢትዮጵያ ንግድ መስመር፣ ቱርዝም፣ እንቨስትመንት ፣ቴክኒካል ድጋፍ ፣ እርዳታ፣ እንድቋረጥ በማድረግ በኢትዮጵያ ፖለትካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀዉስ ለማስከተልና የአገርቱን ህልዉና አደጋ ላይ ለመጣል ከግብፅ፣ ኤርትራ እና አልሻባቢ ጋር በማበር ለተቀን የሚረባረቡ ሃይሎች ተበራክቷል። ስለዚህ መላዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የዉጫዊያን  ክሶች ለማክሸፍና እናት አገርን ለመደገፍ እንቁም!

አመሰግናለሁ!

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርካት!

ዘካሪያስ ጣሎ አንጁሎ

Email zeketalo@yahoo.com